የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፬ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 41
ADDIS ABABA 11th July, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፮/፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በተመረጡ የትኩረት መስኮች የተደረገው የልዩ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ...................................ገጽ ፯ሺ፬፻፳፰

CONTENTS

Proclamation No. 836/2014

Special Status Agreement Between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya on Areas of Agreed Priorities Ratification Proclamation.............. Page 7428

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፮/፳፻፮

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በተመረጡ የትኩረት መስኮች የተደረገውን የልዩ ትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በተመረጡ የትኩረት መስኮች የልዩ ትብብር ስምምነት ህዳር ፲፪ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም በናይሮቢ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 836/ 2014

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE SPECIAL STATUS AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF KENYA ON AREAS OF AGREED PRIORITIES

WHEREAS, the Special Status Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya on Areas of Agreed Priorities was signed in Nairobi on the 21st day of November, 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 8th day of April, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በተመረጡ የትኩረት መስኮች የተደረገው የልዩ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፴፮/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በተመረጡ የትኩረት መስኮች ህዳር ፲፪ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም በናይሮቢ የተፈረመው የልዩ ትብብር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የንግድ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፬ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Special Status Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya on Areas of Agreed Priorities Ratification Proclamation No. 836/2014".

**2. Ratification of the Agreement**

The Special Status Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya on Areas of Agreed Priorities signed in Nairobi on the 21st day of November, 2012 is hereby ratified.

**3. Powers of the Ministry of Trade**

The Ministry of Trade is hereby empowered to undertake, in collaboration with the relevant government organs, all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of July, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት